# የዐማራ ሽግግር ምክርቤት ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ

## ጉዳይ፡ ከዐማራ የሽግግር ምክርቤት ጊዜያዊ አደራጅ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

የዐማራ የሽግግር ምክርቤት ጊዜያዊ አደራጅ ኮሜቴ በምድር ላይ የሕልውናውን ትግል በማንቃሳቀስ፣ በመታገል፣ በመምራት የሕይወት መስዋዕትነትን ጭምር በመክፈል ላይ ያሉ የመላዉ አማራ የሕልውና ታጋዮች አንድ አቀናጅ መዋቅር እንዲመሰረትላቸው በጠየቁት መሰረት፤ “August 23, 2023” ***የአማራ የሽግግር ምክር ቤትን*** ለማዋቀር የሚያስችል የተሳካ ቅድመ ኮንፈረንስ ተደርጓል። የህልውና ትግሉ በሚታገዝበት ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ውይይት ከተኪያሄደ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓበይት ጉዳዮች እንዲተገበሩ ያግዙ ዘንድ የተለያዩ የባለሙያተኞች የሥራ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም ወስኖ ሥራውን ጀምሯል። ***የእነዚህ የሥራ ኮሚቴዎች ዋንኛ ተግባራቸው በቅርብ ቀን ሊደረግ የታቀደውን የአማራ የሽግግር ምክር ቤት የምስረታ ጉባኤ ማዘጋጀት ነው።***

1. የዐማራዉን የሕልውና ትግል በአንድና በተደራጀ መልኩ ብሎም ሕብረትንና አንድነትን በአማከለ የዕዝ ሰንሰለት መምራት፣ ማደራጀትና ሥር ነቀል የሥርአት ለውጥ በማምጣት እንዲጠናቀቅ ማስቻል።
2. የዐማራውን የሕልዉና ትግል ስኬታማ ለማድረግ በተለያዩ የዐማራ አደረጃጀቶች የየራሳቸውን አስተዋፅዖ እያደርጉ ያሉ ሁሉ ተቀራርበው እንዲሰሩና ለሕልውናው ትግልና ለዘላቂው ዓላማችን ተፈፃሚነት እንዲቆሙ የራሳችንን አስተዋጽኦ ማድረግ። ለዚህም በአማራው ህልውና ትግል ለረጅም ግዜ በአደረጃጀትም ሆነ በግል አስተዋጽኦ ያደረጉ ባለጉዳዮች ውይይት አድረገው፤ ልዩነቶቻቸውን አጥብበው አንደ የጋራ አቅጣጫ እንዲይዙ የውይይት መድረኮች ማዘጋጀት።
3. በዐማራው የሕልውና ትግል በታማኝነታቸውና በቁርጠኝነታቸው የተመሰከረላቸውን ዐማራዎች በማሰባሰብ በተለያዩ ሙያዎች ያገኙትን ብቃት፣ ክህሎትና ልምድ ለትግሉ እንቅስቃሴ በተገቢው ቦታ እንዲያውሉት ማድረግ። በተለያዩ ዘርፎች ዐማራው ብቃት ያላቸው ተቋሞች ባለቤት እንዲሆን መስራት።
4. በዐማራው ላይ የሚደርሱትን የማፈናቀል፣ የመግደል፣ የማሰርና በመዋቅርና በፖለቲካዊ አደረጃጀት ከትህነግ ተምረው በብልፅግና/ኦሮሙማ አገዛዝ በሥራ ላይ በስፊው ያዋሉትን የዘር ጭፍጨፋና የዘር ማጥፋት ለዓለም አቀፍ ሰበአዊ ድርጅቶች፣ የተለያዩ መንግስታቶች እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለስቦችን ማስረዳትና ማሳወቅ።
5. የሕልውና ትግሉ አሁን ከደረሰበት እንቅስቃሴ በተሻለ እንዲመራ ማድረግና ይህንን ትግል ለማኮላሸት ወይም ለመጥለፍ የሚፈለጉ ግለሰቦችንም ሆኑ አደረጃጀቶችን ነቅቶ መጠበቅና በሕልውናው ትግል አደረጃጀቶች ውስጥ ገብተው ትግላችንን እንዳይጠለፉ ተግቶ መስራትና ተጠርጣሪዎችን ማጋለጥ።
6. የዐማራውን የህልውና ትግል ወቅታዊና ዘላቂ ግቦች ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በግልጽ እና ጥልቀት ባለው መልኩ ሰነዶች ተዘጋጅተው ልምድና ብቃት ባላቸው ታማኝ ባልሙያዎች እንዲቀርቡ ማስቻል። በተለይ የዐማራው ትግል አሸናፊ መሆን በአፍሪካ ቀንድ ከፍተኛ መረጋጋትና ሁለገብ እድገትን እንደሚያመጣ የሚያስረዳ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ያከናውናል።
7. የዐማራው የህልውን ትግል በድል ሲጠናቀቅ ትንሳኤን በምታገኘው ታላቂቱ ኢትዮጵያ የሆሉም ነገዶች፣ ማህበረሰቦችና እምነቶች በፍትህዊነት፣ በእኩልነት፣ በነጻነት፣ በሕግ የበላይነትና በመተባበር የሚኖሩባት ሀገር እውን ማድረግ።

በትህነግ ተነድፎ በኦነግ ደጋፊነት በመላው የኢትዮጵያ ግዛት የተዘረጋው፤ በመለስና አብይ መሪነት የተተገበረው አንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለው የዘር ፖለቲካ የሕዝባችንን በፍቅር አብሮ የመኖር ዋስትና አደጋ ውስጥ ከመጣሉም በላይ በማነነቱ ላይ ባነጣጠረ መልኩ ንፁሃን የዐማራ ተወላጆች በግፍ እየተጨፈጨፉና እየተገደሉበት ይገኛል። ይህንንም ስንል በተለይ የዐማራው ሕዝብ የዚህ አስከፊና አደገኛ የፖለቲካ ሸፍጥ ግንባር ቀደም ተጠቂና ሰለባ መሆኑ አሁን ላይ በኦሮመማ/ብልጽግናው የአብይ ሴረኛ አገዛዝ በከባድ መሳሪያ፣ በጦር ጀትና በድሮን የሚደበደቡትና በግፍ የሚገደሉት አማራዎች ጥሩ ምሳሌም ከመሆኑም ሌላ ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው፤ በአሁኑ ሰዓት በዐማራው ምድር ላይ የሚፈፀም የጦር ወንጀል ውሳኔ ነው። ዐማራው ለኢትዮጵያ አገራችን ክብርና ነፃነት ፤ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ በዓለም ደረጃ ሰንደቁን ከፍ እንዳላደረገ፤ ዛሬ ግን በእነዚህ የእናት ጡት ነካሾች - የዕፉኝት ልጆች - ከቀየው እንዲፈናቀል፣ እንዲታሰር፤ ንብረቱ እንዲዘረፍ፣ የመገልገያና የልማት ተቋማቶቹ ሆን ተብሎ እንዲወድሙና ይህም ታላቅ ነገድ እንደ አዉሬ እየታደነ እንዲገደል የፖለቲካውን እርከን በጨበጡት ነፍሰ ገዳይ የዘር ፋሽስቶች እንዲጠፋ ተበይኖበታል።

በአሁኑ ሰዓት ሕዝባችን ህልውናውና መብቱ በየትኛውም አቅጣጫ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱ ለማንም ግልጽ ነው። የዚህ አስከፊ የዘር ጭፍጨፋና የሴራ ፖለቲካ መዳረሻ በአንድ በኩል የአማራን ህዝብ ከኢትዮጵያ ለመነጠልና ታሪካዊ ስፍራውን ለማስለቀቅ ሆን ተብሎ የተሸረበ የጥፋት እርምጃ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አማራን አንገቱን በማስደፋት ከሃገሪቱ የፖለቲካ፣ የኦኮኖሚና ማህበራዊ ፍትህዊ ተሳትፎ በማስወገድ ሁለንተናዊ እድገቱን በማገድ በመብት እኩል ድርሻና እጣፈንታ እንዳይኖረው፤ በተጨማሪም ከነበረበት ጠንካራ የስነ-ልቦና አቅም በማውረድ ተንበርክኮ የሚገዛ ሕዝብ ለማድረግ የተወጠነ ሴራ ነው። በተለይም በኢኮኖሚው ዘርፍ በግብርና ምርታማነት ላይ ገበሬው ምርጥ ዘርና ማዳበርያ እንዲያገኝ በመከልከል፤ ገበሬው በሚያርስበትና ሰብል በሚሰበስብበት ወቅት ወረራ በመፈጽም የዐማራው ህዝብ በሚቀጥሉት አመታት የኢኮኖሚ መሰረቱ ተናግቶ በረሀብ እንዲያልቅ ተደርጓል። የዐማራው አዲስ ትውልድ በትምህርት ዘርፍ ውጤታማ እንዳይሆን ባለፉት ሦስት አመታት በዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና ሂደት ውስጥ፣ በታቀደ ሸፍጥ የዐማራ ተማሪዎች ውጤት እናዳያገኙና የከፍትኛ ትምህርት እድል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የአገዛዙ የትምህርት ፖሊሲ እስራ ላይ ውሏል።

በአሁኑ ሰዓት የዐማራ ሕዝብ እጣ ፈንታ አክራሪ በሆኑ ጥቂት የኦሮሞና የትግሬ ጽንፈኞችና ተባባሪ ዘረኞች መዳፍ ሥር በመውደቁ፤ በመሠረታትና የሕይወት ዋጋ በከፈለላት አገራችን ኢትዮጵያ፤ እንደ አውሬ እየታደነ በግፍ የሚገደለው፣ የሚታሰረው፣ የሚሰደደውና የሚዘረፈው፤ ሀገሪቱ በሙሉ ለዐማራ መንግሥት አልባ ሆናለች። በውሸትና በትርክት ላይ የተመሰረተው አጉራ ዘለል ፕሮፓጋንዳቸው ፈር ለቆ፣ ቂም ጠምቆ፣ በቀል ቋጥሮ አቅሙ በፈቀደ መጠንና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የጥፋት ክንዱን በማን አለብኝነት በአማራ ሕዝብ ላይ በማንሳት ለዓመታት በአርባጉጉ፣ በባሌ፣ በአርሲ፣ በሻሸመኔ፣ በሐረር፣ በጉራፈረዳ፣ በመተከል፣ በአጣዬ፣ እንዲሁም እስካሁን ድረስ በአማራ ደም በጨቀየችው የደም ምድር ወለጋ የተፈፀመውና እየተፈፀመ ያለው የዚሁ ሴራቸው ዋና እና አወንታዊ ማስረጃ ነው። በዐማራው ላይ ጅምላ የዘር ፍጅት እንዲደርስ፣ ከመኖሪያ ቀየው እንዲፈናቀል፣ እናቶችና እህቶቹ እንዲደፈሩ፣ ንብረቱና ልማቱ እንዲወድም ሲወሰንበት፣ ወክለንሃል የሚሉት የብአዴን/ ዐማራ ብልጽግና አመራሮች የዐማራው ህዝብ ቀንደኛ ጠላት በመሆን አጋልጠውና አሳልፈው ለገዳዩና ለአረመኔው የኦሮሙማ/ብልጽግና የአብይ አገዛዝ እንደፍሪዳ ለመስዋዕትነት አቅርበውታል። ዐማራው በእነዚህ በተንኮል የተመረዙ የአገዛዙ ሰዎች የተፈረደበት በምጣኔ ሃብት አቅርቦትና ክምችት እንዲደኸይና እንዲደቅ፣ ለእርዛትም እንዲጋለጥ ብቻ ሳይሆን የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ጨምሮ የብዙ አሰቃቂ ወንጀሎች ሰለባ እንዲሆን በማድረግ ነው።

አሁን ደግሞ በተጠና እስትራቴጂ እና በስፋት አቅደው በሥራ ላይ እየተረጎሙት ያለውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም ለዓላማቸው ተፈፃሚነት አመቺ መንገድ ይፈጥርልናል በሚል የዐማራው ሕዝብና ብቸኛ ጠባቂ የሆነውን **ፋኖ** ትጥቅ ለማስፈታት በሚል ሰበብ መጠነ ሰፊ ጦርነትን ከፍተዋል። ይህንንም እውን ለማድረግ አርባ ሁለት ዙር ያሰለጠኑትን የኦሮሞ ልዩ ኃይልና የገዳይ ክንፋቸውን ኦነግ ሸኔን፣ እንዲሁም የትህነግን ወራሪ ሰራዊት የመከላካያን ልብስ በማልበስ ወደ ዐማራ ክልል ያለምንም ከልካይ የገዳይ ስልታቸውን በማንሳት በሸዋ፣ በወሎ፣ በጎጃምና በጎንደር ክፍለ ሀገሮች መጥነ ስፊ ወረራ ፈፅመዋል፤ በመፈፀምም ላይ ናቸው። በዚህም ኢፍትሓዊ ጦርነት ከበባድ መሳሪያዎችን፣ ድሮኖችን እንዲሁም የጦር ጀቶችን በመጠቀም ሰላማዊና ምንም ያልታጠቁ ሕፃናቶችን፣ እናቶችን፣ አዛውንቶችን በቤታቸው በተቀመጡበት ረሽነዋል፤ አቁስለዋል፣ ሰልበዋል፣ ምላስ ቆርጠዋል፣ በኤችአይቪ እና በሌሎች ወረርሽኝ በሽታዎች በክለዋል፣ በብዙ ሺዎች ከአካባቢያቸውም እንዲፈናቀሉ አድርገዋል። እነኝህ የተጎዱ ወገኖቻችን የህክምና ዕርዳታን ለማግኘት እንዳይችሉ ሆን በሎ በመወሰን የፋሽስቱ አብይ ወራሪ ጦር የህክምና መሰጫ ተቋማቶችን (ሆስፒታሎችን፣ መካከልኛና ዝቅተኛ ክልኒኮችን) በቦምብና በመድፍ እንዲጋዩ አድርጓል። ያም ብቻ አይደለም በጠቅላላው የዐማራ ሕዝብ ለሕክምናም ሆነ ለማንኛውም አስፈላጊ እንቅስቃሴ ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ በአብይ አህመድ አሊ፤ በሽመልሰ አብዲሳና በአዳነች አበቤ ትዕዛዛ ታግደዋል። በተጨማሪም በአገሪቱ መዲና በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት፣ በደብረዘይት፣ እንዲሁም በተለያዩ ከተሞች አማራዎች ላይ ማንነታቸውን መሰረት በማድረግ ያለምንም የፍርድ ቤት ትዕዛዛ ቤታቸው እንዲፈርስና እንዲፈናቀሉ ሆኗል፤ ለጅምላ እስርም ተዳርገዋል። በደብረ ኤልያስ ገዳም በአማራነታቸው ከሰባት መቶ ያለነሱ ካህናት፣ መነኮሳት፣ ጸበልተኞችና ገዳሙ ያሳድጋቸው የነበሩ ሕጻናት በዘግናኝ ሁኔታ ተጨፍጭፈዋል። ካህናትን እና የኦርቶዶክስ ምእመናን በሻሸመኔ እና በብዙ የኦሮምያ አካባቢዎች ተገድለዋል፤ ብዙ አብያተ ክርስትያናት ተቃጥለዋል፤ በተጨማሪም ከ20 ያላነሱ መስኪዶች ተቃጥለዋል።

በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት በአማራነቱ ልክ የለሽ ገፈትና ዘግናኝ ጭፍጨፋ እየደረሰበት የሚገኘው ሕዝባችን በወለጋ-ቄለም፣ ሆሮጉድሩ፣ ጊምቢ፣ መተከልን ጨምሮ በሸዋ፣ በወሎ፣ በጎጃምና ጎንደር በዘር ፍጅትና ጭፍጨፋ ዘሩን የማጥፋት፣ ቁጥሩን የመቀነስና፣ ትውልድን የማደህየት፣ የጥፋት ዘመቻ በተቀነባበረና በተጠና መንገድ በኦሮምማ/ ብልጽግና የአብይ አህመድ ዓሊ አገዛዝ በሰፊው እየተካሂደ መሆኑ በዕጅጉ ያሳስበናል። አሁን ደግሞ ይህ አልበቃ ብሎ ለዚሁ የዐማራ ሕዝብ ሌላ ስውር የጥፋት ድግስ በኦሮሙማ እና በትህነግ ጥምር ወራሪ ኃይላት በወሎና በጎንደር በኩል ሲታቀድለትና ሲሰዘረጋለት እየተመለከትን ነው።

**እኛም የአማራ የሽግግር ምክርቤት አደራጅ ኮሚቴ ከሕዝባችንም ሆነ ከሕዝቡ አብራክ የተገኘው የሕዝብ አለኝታ፣ መኪታና ጠባቂ ፋኖ ጋር በመቆም ይህ የፋሽስት አፓርታይድ ስርአት እስኪወገድ ድረስ በቁርጠኝነት ለመታገል ወስነናል።** በሕዝባችን ላይ የታወጀውን ጦርነት በመቃወም በተጨማሪም ለጠንካራው ትግላችንና ለድሉ ፍፃሜ ሊያበቁን ይችላሉ የምንላቸውን ጥሪዎች በሕዝባችንና በመከታችን በፋኖ ስም ከዚህ በታች እናቀርባለን። ስለሆነም፡-

1. የኦሮምማ/ ብልጽግና የአብይ አህመድ ዓሊ ጨፍጫፊ አገዛዝ በአስቸኳይ በዐማራው ላይ ያዘመተውን ሕገወጥ ወራሪ ጦር እያወገዝን፤ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ የዐማራው ኃይል በተባበረ ክንድ ከሸዋ፤ ከወሎ፤ ከጎጃምና ከጎንደር ባስቸኳይ እንዲያስወጣ እናሳስባለን፣ በተጨማሪም የአማራ አጽመ እርስቶች የሆኑት ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጸለምት፣ ራያ፣ መተከል እና ደራ የኦርሞሙማ / ብልጽግና እና የትህነግ ወራሪ ነጻ ሆነው በእራሳቸው በተመረጡ አካላት እንዲተዳደሩ ይህም እውን እስኪሆን ድረስ የዐማራው የህልውና ትግል ለአፍታም እንዳይቋረጥ እናሳስባለን።
2. በከባድ መሳሪያዎች (ታንክ፣ መድፍ፣ የአጭር ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎች) ድሮኖችና የጦር ጀቶች የሚጣሉና የሚወረወሩ ቦምቦች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚያደርሱት ግድያ ከዘር ጭፍጨፋ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በጦር ወንጀለኝነትና በዘር ማጥፋት የሚያስጠይቁ ስለሆኑ የአብይ አህመድ ዓሊ አገዛዝ ይህንን ከማድረግ በአስቸኳይ እንዲያቆም ዓለም አቀፍ ጫና እንዲኖር እንጠይቃለን።
3. በአዲስ አበባ የሚደረገው የዐማራ የሆኑ ቤቶችን የማፍረስና ዐማራውን ሆነ ተብሎ ለማፈናቀል የሚደረጉ ኢፍትሃዊ ተግባራቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ጫና እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

4. በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች በዐማራ ወጣቶች፣ በዐማራ አንቂዎች፣ በዐማራ ሚድያ ተቋማቶችና በዐማራ ተወላጅ ጋዜጠኞች፣ ላይ እየተፈፀመ ያለውን አፍና፣ እስርና፣ እንግልት በአስቸኳይ ቆሞ፣ የታፈኑትም ያለምንም መዘግየት እንዲፈቱ ዓለም አቀፍ ጫና እንዲደረግ እንጠይቃለን።
5. መላው የዐማራ ሕዝብ በሕልውናው ላይ የተቃጣውን አስከፊ ኢሰብዓዊ እና ማህበራዊ ቀውስ ብሎም ኢፍትሃዊ ጦርነት ለመመከት መዘጋጀት ያለበት እንደመሆኑ መጠን፣ ሁሉም የዐማራ ድርጅቶች ሕዝባችንን በማንቃትና በማደራጀት በደጀንነት አብረው ከሕዝባችን ጎን በፅናት እንዲቆሙ እናሳስባለን።
6. በተለያዩ የዐማራ አደረጃጀት የተሰባሰቡ ድርጅቶች ያላቸውን ልዩነት በማስወገድ ለአንድ ዓላማና ለሕልውናው ትግል በጋራ ለመቆምና የትግሉን ምዕራፍ ለማፋጠን እንዲቻል የዐማራ የሽግግር ምክርቤት ከሁሉም ለዐማራ ሕልውና መከበር፣ ለስር ነቀል የሥርአት ለውጥ ማምጣት መርሀቸው አድርገው ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ቃል እየገባ፤ በትብብር ለመስራት ጥሪውን ያቀርባል።

አማራ በጀግኖች ልጆቹ ክንድ ህልውናውን ያስከብራል!!!
በልጆቿ የተባበረ ኃይል የታላቂቱ ኢትዮጵያ ትንሳኤ እውን ይሆናል!!!

የአማራ የሽግግር ምክር ቤት አደራጅ ኮሜቴ
September 10, 2023 (ጳጉሜ 5፣ 2015 ዓ/ም)